## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

# ግልጽ ደብዳቤ ለዓለም አብያተክርስቲያናት ምክርቤት

**ለሬቨሬንድ ዶ/ር ኦላቭ ፊክስ ትቬት**
**የዓለም አብያተክርስቲያናት ምክር ቤት**
**ዋና ጸሐፊ**
**ጄኔቫ፤ ስዊትዘርላንድ**

******************************************************************************************************************

**"የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ፤ ወደ ድሀ አደጎች እርሻ አትግባ፤ ታዳጊአቸው ጽኑ ነውና፥ እርሱም ፍርዳቸውን ከአንተ ጋር ይፋረዳልና።" (ምሳሌ 23፤10፥11)**

ክቡር ሆይ፤

እኛ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) ስር የምንገኝ ከተለያየ ሃይማኖትና ዘር የተውጣጣንና ለማኅበራዊ ፍትህ የቆምን ኢትዮጵያዊያን ነፃነትን እንደሚሻ ህዝብ ወደ እርስዎ መጥተን ጥያቄያችንን እያቀረብን ሲሆን ሰላም በኢትዮጵያ ሊሰፍን የሚችለው፡ እግዚአብሔር ያከበረው ሰብዓዊነት እንዲሁም የእያንዳንዱ የግል እምነት ሲከበር እንደሆነ እናምናለን።

**በዚህ መሰረት የእምነት ልዩነቶቻችን እንደተጠበቁ ሆኖ ሁላችንም የአብርሃም ልጆች የሆንን የክርስትና፣ የእስልምናና የአይሁድ እምነት ተከታዮች ከ20 ዓመታት በላይ ባስቆጠረው የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በኢትዮጵያ የአምነት ነፃነትና የእምነት ተቋማት ላይ እየፈፀመ ያለውን ግፍና በደል እናሳስብዎት ዘንድ ይህንን ደብዳቤ ልከንዎሎታል፡፡** ይህ አናሳ በሆነው የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) የሚመራው አገዛዝ እስከ ቀበሌ ድረስ በዘረጋው ተቋማት እና የእምነት ድርጅቶች ጭምር በህዝባችን ላይ ይህ ነው የማይባል አፈና እያካሄደ ይገኛል።

**የአገዛዙ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ በሶማሊያና በኢትዮጵያ ውስጥ በዘር ማጥፋት፣ በሰብዓዊ ክብር ላይ በሚፈፀም ወንጀል[i] እና በጦር ወንጀለኛነት፤ የተጠረጠሩ እንደሆነ የተለያዩ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ምርመራ ሪፖርቶች ያረጋግጣሉ።** ይህ አገዛዝ "በፀረ-ሽብር ዘመቻ" ላይ ሁነኛ አጋር በመሆን ከየትኛውም የአፍሪካ አገር የተሻለ እርዳታ ከምዕራባዊያን መንግሥታት በሚቀበለው ገንዘብ የራሱን ዜጎች ህዝቡን በማሸበር፣ የተለየ ሃሳብ ያላቸውን በማፈን፣ በእምነት ነፃነት ጣልቃ በመግባት፡ የጎሳና የሃይማኖት ልዩነቶችን እንደመሳሪያ በመጠቀም ግጭቶችን በማቀጣጠል፣ የትውልድ መሬትን፣ የተፈጥሮ ሃብትና ማዕድናትን እንዲሁም ብሔራዊ ሃብትን በመመዝበር የወደፊቱን የትውልድ ተስፋ በማጨለም ላይ ይገኛል።

ይህ ሁሉ አልበቃ ብሎት "ለም ሆኖ ስለተገኘ ስኳር እናለማበታለን" በሚል ጥንታዊ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ገዳማት እና 18 አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙበትን የተቀደሰ ቦታ በመመንጠርና የአምልኮ ሥፍራዎቹ በማፈራረስ ሥራ ላይ ተጠምዶ ይገኛል፡፡ **የዚህ አፍራሽ አገዛዝ ዕቅድ ሰለባ ከሆኑት አንዱ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኘውና በአፍሪካ ካሉ ጥንታዊ ገዳማት አንዱ የሆነው የዋልድባ ገዳም ይገኝበታል።** በገዳሙ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ከሺህ በላይ መነኮሳትና እጅግ በርካታ ክርስቲያኖች የአምልኮ ስርዓታቸውን ለማካሄድ የሚያስቸላቸውን ቦታ በመነጠቃቸው ለመፈናቀልና ለስደት ተዳርገዋል። ጥንታዊውን ገዳም የከበቡና ዘመናትን ያስቆጠሩ የተፈጥሮ ደኖች ይጨፈጨፋሉ እንዲሁም የተፈጥሮ ሞገስ የሆኑ አዕዋፋት ይሰደዳሉ። ከዚህ በተጨማሪም በቅርቡ ጥንታዊው የዝቋላ ገዳም ምስጢራዊ በሆነ መንገድ ለቃጠሎ የተዳረገ ሲሆን የአካባቢው ነዋሪ እሳቱን ለማጥፋት ያደረገው የድረሱልን ጥሪ ሰሚ ያጣ ሆኖ ቀርቷል፡፡ በአንጻሩ ግን የተለያዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ይህም አካባቢ "ለልማት የተፈለገ ቦታ" በመሆኑ ቃጠሎው አካባቢውን ከመመንጠር ጋር የመያያዝ ባህርይ እንዳለው ያሳያል፡፡ ከዚህ ሁሉ ጋር አክሎም ለዘመናት የቆዩ የመቃብር ቦታዎች በቡልዶዘር እየተቆፈሩ በመውጣት አካባቢው ረክሷል፡፡

አገዛዙ በሚፈጽማቸው በእነዚህ ሁሉ ድርጊቶች፡ በዋጋ የማይተመኑ ንዋየ ቅዱሳትና መገልገያዎች ሲወድሙ የእምነት ተቋማት እጅጉን እየተዳከሙ መጥተዋል፡፡ የሕዝባችን ልብ ደምቷል፡ ህመሙን መሸከም ተስኖት ሞራሉ ወድቋል። የህወሃት/ኢ.ህአዴግ አገዛዝ ጥንካሬውን የሚያሳየው እነዚህን የህዝብ የእምነት ተቋማት በማውደምና በማንኛውም ጉዳይ ላይ አዛዥ ናዛዥ እርሱ ብቻ መሆኑን በኃይል በማሳየት ሆኗል።

**ይህ ዓይነቱ ድርጊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮችን በእጅጉ ያስቆጣ ሲሆን አገዛዙ የእምነት መሰረት የሆኑና ከሺህ ዓመታት በላይ ያስቆጠሩ የእምነት ስፍራዎችንና በውስጡ የሚገኙትን ታሪካዊ ቅርሶችን ጭምር በግዴለሽነት ለማውደም የሚገድበው ነገር እንደሌለ ለሌሎች የክርስትና፡ የእስልምና፡ አይሁድ እምነት ተከታዮች፡ ማስጠንቀቂያ የሰጠም ነው።**

ለእምነታቸው ትልቅ ትርጉም በመስጠትና በመጠበቅ ኢትዮጵያውያን ቀዳሚነት ያላቸው ናቸው። **በብሉይ ኪዳን ከዘፍጥረት ጀምሮ ኢትዮጵያ (ኩሽ) የተጠቀሰ ሲሆን ሙሴ ያገባው ኢትዮጵያዊት መሆኗን እንዲሁም የነብዩ ኤርምያስን ህይወት ያዳነው ኢትዮጵያዊ ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ከየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት መካከል አንዱ በሆነው አማካኝነት ኢትዮጵያ የወንጌልን መልዕክት ለማግኘት የቻለች ሲሆን በዚህም ከአፍሪካ ቀደምት የክርስቲያን አገር ልትሆን ችላለች፡፡ የገዳማቱና አብያተ ክርስቲያናቱም ጥንታዊነት የዚህ ጉልህ ማስረጃ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም - እስልምና በመካከለኛው ምስራቅ እየተስፋፋ ሲመጣ ሙዕሚኑ በወቅቱ ስደት በደረሰባቸው ጊዜ ጥበቃና ከለላ ሊያገኙ የሚችሉት በኢትዮጵያ ንጉሥ ሥር መሆኑን በመግለጽ ነብዩ መሐመድ (ሰአወ) ወደዚያው ሄደው እንዲሸሸጉ ምክር በሰጧቸው መሠረት ኢትዮጵያ መጥተው ከለላ በማግኘት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ተቻችለው፣ ተዋደውና ተከባብረው በሰላም ለመኖር በቅተዋል፡፡**

ሆኖም ይህንን የመቻቻልና አብሮ የመኖርን ህይወት በማዳከም በተለያዩ እምነት ተከታዮች መካከል ግጭት በማቀጣጠል የተጠመደው የህወሓት/ኢ.ህአዴግ አገዛዝ እየተዳከመ በመሆኑ የእምነት ልዩነቶችንና ግጭቶችን ለዜጎች መከፋፈያና ለራሱ ዕድሜ ማራዘሚያ መሳሪያ አድርጎ በመጠቀም ላይ ይገኛል። በውጤቱም የሃይማኖቶችን መቻቻል በማዳከምና ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች ባልታወቁ አካላት እንዲቀጣጠሉ በማድረግ ለህይወት መጥፋት ምክንያት ከመሆኑም በላይ አገሪቱ አጣቢቅኝ ውስጥ በገባችበት በዚህ ሰዓት በእጅጉ የሚያስፈልጋትን የሃይማኖት መሪዎች ጥንካሬና የእምነት ነፃነት አዳክሟል። በመሆኑም የስኳር ልማቱ "ለሕዝብ ልማት ነው" ተብሎ ቢነገርም ልማቱ የሚጠቅመው ግን የአገዛዙን ቁንጮዎችና ቤተሰቦቻቸውን ሊሆን እንደሚችል የብዙዎች እምነት ነው።

ኢትዮጵያዊያን በገዛ አገራቸው ጉዳይ ገለል ተደርገው መሬታቸውና የተፈጥሮ ሃብታቸው እንደ ህንድ፡ ሳውዲ አረቢያ፡ እና ቻይና ለመሳሰሉ የውጭ ባለሃብቶች እየተሸጠ ይገኛል። ምንም እንኳን ይህ የመሬት ነጠቃ በሌሎች የአፍሪካ አገሮች እየተካሄደ ቢሆንም ኢትዮጵያ የዚህ ድርጊት ዋንኛ ሰለባ መሆኗን እና ህዝቡ ሳይመክርበትና ምንም አይነት ካሳ ሳይከፈው መሬቱን እየተነጠቀ መሆኑን የኦክላንድ ተቋምና ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ በጋራ ያወጡት ዘገባ ያረጋግጣል[ii]። የሰብዓዊ መብትን የሚከታተለው (ሂዩማን ራየትስ ዎች)[iii] በጋምቤላ ባካሄደው ምርመራ 70ሺ. ደሃ ገበሬዎች ከኖሯቸው ተፈናቅለው መሬታቸው ለ99 ዓመታት በሊዝ ለውጭ ኩባንያዎች መሸጡን አረጋግጧል፡፡ **ይህ ሽያጭ ከተደረገላቸው ኩባንያዎች መካከል አንዱ 100ሺ. ሄክታር የለማና በውሃ የተከበበ መሬት የተሰጠው የህንዱ ካሩቱሪ ግሎባል የተባለው ኩባንያ ሲሆን በአጠቃላይ 300ሺ. ሄክታር መሬት በ1.20 (በአንድ ዶላር ከሃያ ሳንቲም) ሂሳብ ለመከራየት የሚያስችለው ቃል ተገብቶለታል።**

**በ2010 እ.ኤ.አ. በሚኒሶታ ዩኒቨርሲቲ[iv] ይፋ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው በ2009 እ.ኤ.አ. በሚኒሶታ ለአንድ ሄካታር መሬት እስከ 150 የአሜሪካን ዶላር ይከፈል ነበር። ከዚህ አንጻር ካሩቱሪ በጋምቤላ የወሰደው 300ሺ. ሄክታር ለም መሬት በአንድ ሄክታር 1.20 ዶላር ሂሳብ ሲሰላ የሚመጣው 360ሺ. ዶላር ብቻ ሲሆን ይኸው 300ሺ. ሄክታር መሬት በሚኒሶታ በሄክታር 150 ዶላር ስሌት ዋጋው 111 ሚሊዮን 191ሺ. 400 ዶላር ($111,191,400) ይመጣል፡፡** ፍትሃዊ ለመሆን ያህል በጋምቤላው መሬት ካለው የፖለቲካ ሁኔታና የመሰረተልማት አለመስፋፋት አኳያ መነሻ የኪራይ መጠኑ ከሚኒሶታው አንፃር ማነስ ያለበት ቢሆንም አሁን ግን ያለው የተጋነነ ልዩነት የሚያሳየን የአፍሪካን መሬት ለመቀራመት ያለውን እሽቅድምድምና ውጤቱም የህዝብን ስቃይና ሰቆቃ እንዴት እንደሚያበራክት ነው።

መሬቱን ለተበረከተላቸው የውጭ ኩባንያዎች ሁኔታውን ምቹ ለማድረግና ያመረቱትንም ሰብል በችጋር ህዝቧ ከሚማቅቅባት አገር ነጥቀው ወደ ውጭ ሃገር ለመላክ እንዲችሉ 3/4ኛ የሚሆነው የአካባቢው ትላጅ ኅብረተሰብ በኃይልና ህገወጥ በሆነ መንገድ ለዘመናት ከኖረበት መሬት እየተፈናቀለ ይገኛል፡፡[v] የህወሓት/ኢ.ህአዴግ አገዛዝ "የውሃ አቅርቦትና ሌሎች አገልግሎቶች እናሟላለን" እያለ በሚገባው አታላይ ቃል ተታልለውና ተጽዕኖ ተደርጎባቸው ጥቂት ነዋሪዎች ሌላ አካባቢ ለመስፈር የተስማሙ ቢሆንም የተገባላቸውም ቃልኪዳንና የተሻለ አገልግሎትም ሆነ መሰረተልማት እውን ሲሆን አልታየም፡፡ ተታልለው የተፈናቀሉት የቀራቸው ነገር ቢኖር በአጅግ አነስተኛና ውሃ በሌለው መሬት ላይ ተወስነው መቅረት ብቻ ነው። በሁኔታውም ከፊሎች ሲሞቱ ድርጊቱን የተቃወሙ ደግሞ የአገዛዙ አሰቃቂ ሰቆቃ ተጠቂ ሆነዋል። ይህ

እየተከሰተ ያለው በበርካታ የኢትዮጵያ ክፍለሃገራት ሲሆን አሁን ደግሞ ጥንታዊውና ታሪካዊው ገዳም የዚህ ኢላማ ሰለባ እየሆነ ይገኛል።

በሰሜን አሜሪካ የሚገኘው የኢትዮጵያዊነት ውርስና ቅርስ ማኅበረሰብ ገዳሙን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ **"በጎንደር የሚገኘው የዋልድባ ገዳምና መሬቱን ለማፍረስ እየተደረገ ያለውን መስማታችን እጅግ አስደንጋጭ ነገር ሆኖብናል፡፡ ገዳሙ ከጥንታዊ የኢትዮጵያ የትምህርት ተቋማት አንዱ ሲሆን በላፉት ሺህ ዓመታት ተቆጥረው የማያልቁ የሃይማኖት አባቶችና መሪዎች በቅፅረ ግቢው ተምረዋል። ገዳሙ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና ለኢትዮጵያ ሃይማኖትና ታሪክ ጠቃሚ የሆኑ ቅርሶችንና በጥንታዊ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የተፃፉ መጻሕፍትን፡የያዘ ነው"** ብሏል፡፡

ጠቃሚ የእምነት ስፍራዎች ከሚደረግላቸው ጥበቃ በተጨማሪ ብሄራዊና ዓለም አቀፍ ታሪካዊ ቅርሶችም ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል። **በተወሰኑ ክልሎች የሚገኙ አንዳንድ ገዳማትና ቤተክርስቲያናት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (በዩኔስኮ) እና ዓለም አቀፍ ህግ ጥበቃ አግኝተዋል። ሆኖም አሁን በኢትዮጵያ እየተከናወነ ያለው ነገር በአፍጋኒስታን በአልቃይዳ ከወደሙት የእምነት ስፍራዎች የተለየ ባለመሆኑ ጥብቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ብቻ ሳይሆን እንዲሁም ፈፅሞ እንዲከሰት መፈቀድ የለበትም።**

የህዝቡን ቁጣ የተመለከተው የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ "ልማቱ ገዳሙን አይጎዳም" የሚል መግለጫ የሃይማኖቱ መሪዎች እንዲሰጡ ያደረገ ሲሆን እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ግን የአገዛዙ አምሳያ የሆኑ ስልጣን ላይ ካለው የህወሓት ጎሳ አባል የሆኑና ዋልድባንም በቅጡ የማያውቁ ናቸው። ይህ አገዛዝ ጠንካራ የሃይማኖት አመራርን ለስልጣኑ ጠላት አድርጎ የሚመለከት በመሆኑ ከዓመታት በፊት በኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሪዎች መካከል መከፋፈልን ከፈጠረ በኋላ ቁልፍ የሆኑ መሪዎችን ለራሱ በሚመቹ የሃይማኖት መሪዎች መተካቱ የሚታወስ ነው። **በአሁኑ ጊዜ የቅዱሳን አባቶችን አፅም በቡልዶዘሮች መቆፈር የጀመረው ይህ አገዛዝ ከህዝቡ ጠንካራ ተቃውሞ ቢገጥመውም በቃል አቀባዩ አማካኝነት በሰጠው መግለጫ ጉዳዩን የማጣጣልና ተራ የማድረግ ሲሆን "የሙታን አፅም በሰባት ዓመታት ውስጥ የሚፈራርስ ከመሆኑ በተጨማሪ ያሉትም ቢሆኑ ወደ ሌላ አካባቢ ተወስደዋል፤ ይህ ተራ ክስ ነው" የሚል አሳፋሪ መልስ ሰጥቷል።**

በቅርቡ የኤርትራ ጋዜጠኛ የሆነችው **ሶፊያ ተስፋማሪያም ከ1998-2000 ዓም** (እኤአ) በተከሰተው የድንበር ግጭት ወቅት ህወሓት/ኢህአዴግ ተመሳሳይ ተግባር መፈጸሙን *ERITREA: Meles Zenawi's Lower Case Treachery* በሚለው ጽሁፏ ላይ ስትገልጽ **"የመለስ ወታደሮች አብያተክርስቲያናትንና መስጂዶችን አውድመዋል፤ መጽሐፍ ቅዱስና ቁርዓንን ጨምሮ ቅዱሳን መፅሃፍትን አቃጥለዋል። ወታደሮቹ ከሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በታሪካዊነቱ የታወቀውንና ከሰንዓፌ ከተማ ሁለት ኪሎሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን የበለው-ከለው ታሪካዊ ሃውልቶችን አውድመዋል። ከሁሉም በላይ ግን የኤርትራ ሰማዕታት ያረፉበትን የመቃብር ስፍራ ማውደማቸው እጅግ አስቀያሚና ትርጉም የለሽ የሆነው ተግባራቸው ነው፡፡ የዚህ አናሳ ቡድን ወታደሮች የሰማዕታቱን ኃውልት በመቆፈር የሬሣ ሣጥኖችን ዘርፈዋል፡፡ ለሰማዕታቱ ክብር የተተከሉትን ዛፎችም አውድመዋል፤ አጥንቶቻቸውን አፈራርሰው በየሜዳው በታትነዋል፡፡ ይህንንም በማድረግ አገዛዙ ለኤርትራዊያን ያለውን ጥላቻና ለሞቱ ሰማዕታት ኤርትራዊያን እንኳን ሳይቀር ያለውን ንቀት አሳይቷል።"**[vi] በማለት የአገዛዙን ስነ-ምግባር የጎደለው ድርጊት ዘግባ ነበር።

በመሃል አዲስ አበባ የሚገኘው የቅዱስ ዮሴፍ የመቃብር ቦታ ለሳዑዲው ቢሊየነር ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ የሪል እስቴት ግንባታ ፍላጎት ብቻ ሲባል እንዲፈርስ ተደርጓል[vii]። በጋምቤላም እንዲሁ የመቃብር ቦታ ለካራቱሪ ግለሎባል እርሻ ሲባል በቡልዶዘር እንዲፈርስ ተደርጓል። እነዚህ ሁሉ ዓለም አቀፍ ህግጋትን የሚጥስ በኢትዮጵያዊያን ማንነት ላይ የተቃጡ ድርጊቶች አገዛዙ ለታሪክና በታሪክ ለተሰው ሙታን ያለውን ዝቅተኛ ክብር የሚያሳይ ነው። ይህ በሕዝብ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶች ላይ የሚቃጣ እርባና ቢስ ድርጊት ህዝባችንን በአንድነት የሚያነሳሳ የልቅሶ ጅማሬና የፖለቲካ ምህዳር ብቻውን ሊፈታው የማይችለው ነገር የህዝቦች የጋራ እምነት ሊፈታ እንደሚችል ማሳያ ሆኖ ሊታይ የሚችል ነው፡፡

የመሬት ባለቤትነት መብት በሚጣስበት ወቅት በሃይማኖት ተቋማትና ተቀባይነታቸው በጎላ ባህሎች ላይ የሚቃጣው ድርጊት አገዛዙ እንደ አፓርታይድ ስርዓት የራሱን ጎሳ፣ ክልልና ደጋፊዎች ብቻ ከመደገፉ ጋር ተያይዞ የጎሳ ግጭቶች ሊከሰቱ ይችላሉ የሚል ስጋት እየጨመረ መጥቷል። በኢትዮጵያ ያለው የመሬት፣ የተፈጥሮ ሃብት ነጠቃና የክፍፍል ሽሚያው በምዕራባዊያን አንዳለው ህዝብን ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢኮኖሚ ልማት የሚያመጣ ሳይሆን አንድ አገዛዝ በዓለማችን ደሃ ከሆነው ህዝብ የሚነጥቅበት ሂደት ነው። በአሁኑ ጊዜ አገዛዙ ሥር በሰደደው የፖለቲካ ስርዓት፣ ፍትሃዊ ባልሆነ ምርጫ፣ ጠያቂነት በሌው የሰብአዊ መብት ጥሰት የፈለገውን በእጁ በማስገባትና ስር በሰደደው ሙስና በማታለል ጥቂቶች የአናሳ ልሒቃን ሃብት እያከማቹ ሲሄዱ ብዙሃኑ ግን በድህነት አዘቅት ውስጥ ገብቶ መከራውን እያየ ይገኛል።

**በቅርቡ "Global Financial Integrity"[viii] የተሰኘው ድርጅት ይፋ ያደረገው ጥናት እንደሚያሳየው ይህ የመሬት ንጥቂያ በተጀመረበት እ.ኤ.አ. 2009 ዓ.ም. በሙስና፣ በጉቦ፣ በማጭበርበርና ንቅዘት ከኢትዮጵያ ይወጣ የነበረው የገንዘብ መጠን 3.26 ቢሊዮን አሜሪካን ዶላር ሲሆን ወደ ውጭ የተላከው የምርት መጠን**

**ግን 2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ብቻ እንደሆነ ያትታል።** ሪፖርቱ ሲቀጥልም **"የኢትዮጵያ ህዘብ ደረቅ ደም እያፈሰሰ ነው፤ ሕዝቡ ከድህነትና ጉስቁልና ለመውጣት ምን ቢለፉም የእነርሱ ልፋትና ወደ ውጭ የሚፈሰው ገንዘብ ሲታይ ወደ ዳገት የመዋኘት ያህል ነው"**[ix] በማለት የነገሩን ውስብስብነት ከማጋለጥ ባለፈ መልኩ አስተያየቱን ይሰጣል።

በህወሓት አገዛዝ የኢትዮጵያ ሃብት በሁሉም መስክ እየተዘረፈ ይገኛል - መሬታችን፣ ልጆቻችን፣ ሴቶቻችን፣ ተስፋችን - ማንኛውም አይነት የከሰረ አገዛዝ የሚያተርፈው ዓይነት ትርፍ እየተተረፈብን ይገኛል። ልጆቻችን በእርግጥም ወላጅ አልባ ሆነው ሳይሆን በአገዛዙ ውስጥ ያሉት ግለሰቦች ከህግ በላይ በመሆናቸው ብቻ ህፃናቶቻችን በውጭ ለሚገኙ አሳዳጊዎች እንደ ዕቃ እየተነገደባቸው ይገኛል።[x]

ሴቶቻችንን ብንመለከት ወጣትና በድህነት ሰቆቃ ውስጥ ያሉ ወጣት ሴቶች ለቤት ሰራተኛነት በሚል ብዙዎች ለቤት ውስጥ ባርነት፣ ለአካላዊ ጥቃት፣ ለወሲባዊ ጥቃትና ራስን ለማጥፋት አንዳንዴም በአሰሪዎቻቸው ከእንስሳ ባነሰ ሁኔታ ተገድለው ወደሚቀሩበት[xi] የመካከለኛው ምስራቅ ሊባኖስ፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ሊቢያ እና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ የመላክ ስራ ለኢትዮጵያ አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች እንደ "ኤክስፖርት" ቢዝነስ የሚታይ ነገር ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝም በወር 45ሺ ሰራተኞችን ወደእነዚህ ሃገራት ለመላክ እቅድ አንዳለው በራሱ ድረ-ገፆች ላይ እያስነበበ ወደ እነዚህ ሃገራት በኤጀንሲዎች ሰራተኞችን የመላክ ስራ ተከልክሏል እያለ በሌላ በኩል የሚናገረው ትርጉም የሚሰጥ ነገር አይሆንም።[xii]

በአሁኑ ወቅት ሁሉም ሰው ከኢትዮጵያ መውጣት የሚፈልግበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፤ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ኑሮ ለአብዛኛው ህዝብ ከአቅም በላይ ስለሆነ ነው። Oxford Poverty and Human Development Initiative (OPHI)[xiii] **በተሰኘው እ.ኤ.አ. በ2010 የተካሄደ ጥናት ኢትዮጵያ አሁንም የዓለማችን ሁለተኛ ደሃ አገር ስትሆን የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ግን የሁለት አኻዝ የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግበናል ይላል፡፡** ይህ የህወሓት የመከራከሪያ ነጥብ እርግጠኛ ከሆነ ስለምንድን ነው እጅግ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ሌላ አማራጭ ፍለጋ ህይወታቸውን ለአደጋ እያጋለጡ ከአገራቸው ለቅቀው የሚወጡት? ብዙዎች ወደ ሌላ ሃገር ለመሻገር ያላቸውን ንብረት ሁሉ ሸጠው ለህገ ወጥ ሰው አዘዋዋሪዎች ይከፍላሉ፡፡ ሆኖም ከነዚህም መካከል ብዙዎች በመንገድ ይሞታሉ፤ ተጭነውባቸው የሚሄዱት ከአቅም በላይ የተጫኑ ጀልባዎች በባህር ውስጥ ሰምጠው ይቀራሉ፤ በታጨቁ ኮንቴነሮች ውስጥ አየር አጥተው ታፍነው ይሞታሉ፡፡ ይህ ብቻ አይደለም እነዚህ ወገኖቻችን በሰሃራ በረሃ ውስጥ ሲሞቱ በህገ ወጥ አዘዋዋሪዎቻቸው የሰውነታቸው ክፍሎች እየተወሰዱ ለንግድ ይቀርባሉ፡፡ ይህንን ከቤተሰቦቻቸው፡ ከጓደኞቻቸውና እንደ ማሊ ሐይቅ ባሉና በሌሎች አገራት የሙት የኢትዮጵያዊያን ሬሳ ከሚንሳፈፍባቸው አገሮች በማስረጃ አረጋግጠናል።

ኢትዮጵያዊያን በአገራቸው ውስጥም ሆነ ከአገራቸው ውጭ አደጋ ውስጥ ያሉ ናቸው። በተመሳሳይ ወቅት ረሃብ እና የሩዋንዳ አይነት የዘር ጭፍጨፋ የመከሰት ስጋት[xiv] እያንዣበበ ይገኛል። ይህ ሁሉ የኢትዮጵያ ሃገር ግንባታ መውደቅን የሚያስከትል ሲሆን ድምር ውጤቱ ደግሞ የምስራቅ አፍሪካ ቀጣናን በበለጠ ወዳልተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ የሚያስገባ ነው። ይህ ነገር እንዳይከሰት ካስፈለገ ትርጉም ያለውና ነፃነት፣ ፍትህ፣ እርቅና እኩልነትን የሚያረጋግጥ ተግባር መፈጸም የግድ ይላል፡፡

የሃይማኖት መሪዎች ራሳቸውንና ህዝቡን እርስ በርስም በፈጠራቸው አምላክ አምሳያ በመተያየት **ከዘር ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ በመስጠት** በመንገድ ላይ የወደቀውን ሰው ለመርዳት ዘሩን፣ ሃይማኖቱን፣ የፖለቲካ አመለካከቱን ወይም አገሩን እንዳልጠየቀው የመፅሃፍ ቅዱሱ መልካሙ ሳምራዊን አርአያነት የሚከተሉ እንዲሆኑ እንፈልጋለን። በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ይህ የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከዚህ በተቃራኒው ኢትዮጵያውያንን በዘርና በሃይማኖት በመከፋፈል ጥላቻና እርስበርስ መናቆርን ለመፍጠር ሌት ተቀን እየሰራ ይገኛል።

ህወሓት ወደ ሥልጣን ከመምጣቱ በፊትና በበረሃ በነበረበት ጊዜ ጨካኝ፣ አሸባሪ፣ የማርክሲስት-ሌኒንስት ፍልስፍና የሚያራምድ ስለነበር በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት እንደ አሸባሪ ድርጅት መመደቡ ይታወሳል። ህወሓት ሌሎችን ተጠያቂ ለማድረግ የራሱን ሰዎች ይገድል ነበር፡፡ የውጭ አገር ሰብዓዊ እርዳታ ሰራተኞችንና ሚሲዮናዊያንን አፍኗል፤ ገድሏል። በቅርቡ የዊኪ ሊክስ (ሹልክዓምድ) ይፋ እንዳደረገው እኤአ በ2006ዓም የህወሓት/ኢህአዴግ የፀጥታ ኃይሎች ሶስት ቦንብ ፍንዳታዎችን በአዲስ አበባ ማቀነባበራቸውን ይፋ አድርጓል። በዚያን ጊዜም ድርጊቱ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ጨካኝ ድርጊት ተደርጎ የቀረበ ሲሆን ከፊሎች ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ ታስረዋል[xv]።

ይህ ብቻ አይደለም፤ የኦሮሞ ህዝብ የዚህ አገዛዝ ዋነኛ ዒላማ ከሆነ ዓመታ ተቆጥረዋል፡፡ በቁጥር ከፍተኛውን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚይዘው የኦሮሞ ሕዝብ ሲሆን በተቃራኒው በህወሓት ለሞት ተዳርጓል፡፡ በተለይ በሃይማኖትና ሌሎች ልዩነቶች አጅግ ብዙ ጊዜ ህዝቡን ለመከፋፈል ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። በሌላ ጊዜ እ.ኤ አ. በ2006 አቶ መለስን የሚደግፉ ሙስሊም ኦሮሞዎች በክርስቲያኖች ላይ አምልኮ እያደረጉ በነበሩበት በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደተገደሉ ይታወሳል። ጉዳዩ የቀረበው በተለያየ መልኩ ሲሆን የጋራ ንቅናቄያችን፡ ለተቀሩት ክርስቲያኖች በተለይም ለአንድ እህታችን ያልነው ነገር ቢኖር ጥቃቱን አደረሱ

ከተባሉት አንደኛው የራሳቸው ወገን አንደሆነ ነበር። እህታችን የተባለው ሰው የርሷ ዘመድ ይሁን እንጂ ሙስሊም አይደለም ብላ ነበር፡፡ በኋላ ግን ጉዳዩ ሲጣራ ዋነኛ የህወሓት/ኢህአዴግ ተባባሪዎች መካከል አንዱ ነበር። ይህ ዓይነቱ ድርጊት ምዕራባዊያን የበለጠ እርዳታና ድጋፍ እንዲሰጡ የሚያደረግ በሰው ልጅ ደም በማታለል የተሞላ ጭካኔያዊ ተግባር ነው። ኦሮሞዎችን በሃይማኖት በመከፋፈል ለመግዛት በሚደረገው ጥረት ከዚህ በፊት ባልነበሩና በሃይማኖቶች መካከል በሚፈጠሩ ግጭቶች ላይ ቤንዚን እያርከፈከፈ ይገኛል። ህዝቡ ምስጋና ይግባውና እንዲህ ያለውን እኩይ ተግባር ብዙዎች እምቢ ብለዋል፡፡ ሆኖም ጥቂቶችን ለሃገሪቱ፡ ለቀጣናው ምስራቅ አፍሪካና ዓለም ሰላም አደገኛ ሊሆኑ በሚችሉበት ሁኔታ ፅንፈኞች አድርጓቸዋል፡፡

**እየተካሄደ ያለው የሚያሳስበው ጉዳይ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ብቻ አይደለም፡፡ ሁሉንም ክርስቲያኖች፣ ሙስሊሞችና አይሁዶችን ጭምር እንጂ። ህወሓት/ኢህአዴግ አጅግ አፋኝ የሆኑ ህጎችንም አውጥቷል[xvi]፡፡ ከእነዚህ አንዱ በሆነው ሕግ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን እንዲሁም እኩልነት፡ የፆታና ሃይማኖት እኩልነት፡ የህፃናትና አካል ጉዳተኞች መብት እንዲሁም ግጭት አፈታትና እርቅ ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሁሉ የገቢያቸውን 10 በመቶ በላይ ከውጭ ምንጭ ከተቀበሉ እንደ ወንጀለኛ በህግ ይጠየቃሉ[xvii]። በሕዝብና ሃይማኖቶች መካከል እርቅ የሚሰብኩትን በእስር የሚቀጣ ህግ ያለበት ስርዓት፡ ምን አይነት አገር ይሆን የሚባለው?**

ስለዚህ የዓለም አብያተክርስቲያናት ምክርቤትም ሆነ መላው የእምነት መሪዎች በዚህ የእምነት ነፃነት እና ሰብአዊ መብት ጥሰት ላይ በጋራ ድምፃቸውን እንዲያሰሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን። ጥሪውን የምናቀርበው አፈና እንዲቆም እንደ ማህበራዊ ፍትህ ተከራካሪዎች ወይም እንደ አፍሪካዊያን ወይም ኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን የአንዳችን የመኖር ህልውና በሌላው ላይ እንደተመሰረተ የሰው ልጅ ቤተሰብ ***ሁላችንም ነፃ ካልወጣን ማንም ሰው ነፃ አይሆንም*** የሚለውን ፅኑ እምነታችንን ይዘን ነው።

**ይህን የሁላችንን ጉዳይ ለየመንግስታቶቻችሁ፡ ለማኅበራት ድርጅቶቻችሁ ወይም ውሳኔ ሰጪዎች ለሆኑት ሁሉ እንድታስተላልፉ ጥሪያችንን እናቀርባለን። ይህንን በታሪካዊ የሃይማኖት ገዳም ላይ የሚፈፀም የታሪክ ውድመት፤ ኢፍትሃዊ ድርጊትና ህገ ወጥ የመሬት ነጠቃ በማጋለጥ ከጎናችን እንድትቆሙ ጥሪ እናስተላልፋለን። የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በሃይማኖቶች መካከል የሚፈጥረውን ግጭት እንዲሁም በእምነት ነጻነት ላይ እየፈፀመ ካለው ጣልቃ ገብ የጥፋት ድርጊት እንዲቆጠብ እንድታወግዙ ጥሪያችንን እናቀርባለን።**

ዓለማችን የተሻለ ልትሆን የምትችለው የእምነት ሰዎች እርስ በርስ በመረዳዳትና በጨካኝ አገዛዝ ቀንበር ስር ያሉት በእግዚአብሔር ፍቅር ከተጫናቸው ቀንበር ተላቀው አምላካቸውን እንዲያመሰግኑ ስንረዳ ነው። ፈጣሪያችን ጥንካሬውንና ብርታቱን ሰጥቶ እንዲሁም መንገዱን መርቷችሁ በቅርብም በሩቅም በሰቆቃ ውስጥ ያሉትን እንድትታደጉ የርሱ መልካም ፈቃድ ይሁን።

************************************************************************************************************

**"መበለቶችም ቅሚያቸው እንዲሆኑ፥ ድሀ አደጎችንም ብዝበዛቸው እንዲያደርጉ፥ የድሀውን ፍርድ ያጣምሙ ዘንድ፥ የችግረኛውንም ሕዝቤን ፍርድ ያጐድሉ ዘንድ የግፍን ትእዛዛት ለሚያዝዙ፥ ክፋንም ጽሕፈት ለሚጽፉ ወዮላቸው!" ኢሳይያስ፡10፤1 - 2**

---

በአግዚአብሔር ፍቅር ወንድማችሁ



**ኦባንግ ሜቶ**
**የአኢጋን ዋና ዳይሬክተር**
Email: Obang@solidaritymovement.org.
Website: www.solidaritymovement.org

**ግልባጭ፤**

**ይህ ደብዳቤ ለሮም ካቶሊካዊት ቤ/ክ ሊቀጳጳስ እና በየአገሩ ለሚገኙ አገረ ስብከቶች፤በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ የኦርቶዶክስ ሊቃነ ጳጳሳት፤ ለወንጌላውያን፣ ለሉተራን፣ ለመጥምቃውያን አብያተክርስቲያናት በአጠቃላይ ለ29 የሃይማኖት መሪዎችና ለ12 ዓቢይ የመገናኛ ብዙሃን ተልኳል፡፡**

[i] *See multiple human rights investigations from Genocide Watch and Human Rights Watch.*

[ii] http://www.solidaritymovement.org/downloads/110608UnderstandingLandDealsInAfrica.pdf ; http://www.solidaritymovement.org/110608PressReleasesOnJointReport.php ; Joint Report from Oakland Institute and SMNE Sounds Alarm on Foreign Agri-Investments in Food Insecure Ethiopia

[iii] http://www.hrw.org/reports/2012/01/16/waiting-here-death

[iv] http://minnesota.publicradio.org/collections/special/columns/statewide/archive/2010/11/farmland-rents-rise.shtml

[v] http://www.brecorder.com/world/africa/52084-ethiopias-resettlement-plan-falls-short-on-development.html

[vi] *http://www.eritreacompass.com/eritrean-news/54-politics/643-eritrea-meles-zenawis-lower-case-treachery.html ERITREA: Meles Zenawi's Lower Case Treachery, by Sophia Tesfamariam, November 5, 2011*

[vii] http://www.businessweek.com/news/2012-04-05/saudi-billionaire-to-invest-600-million-in-ethiopia-cooking-oil

[viii] *http://www.financialtaskforce.org/2011/12/05/illegal-ethiopian-capital-flight-skyrocketed-in-2009-to-us3-26-billion/ ; GlobalFinancial Integrity, "Illicit Financial Flows from Developing Countries over the Decade Ending 2009," by co-author, SarahFreitas, December 2011*

[ix] *Ibid*

[x] http://www.theatlantic.com/international/archive/2011/12/how-ethiopias-adoption-industry-dupes-families-and-bulliesactivists/250296/

[xi] http://english.alarabiya.net/articles/2012/04/06/205839.html Video news: Housemaid's Death Rattles Lebanon's Conscience http://www.chicagotribune.com/news/sns-rt-us-lebanon-housemaidbre8330vr-20120404,0,4849757,full.story

[xii] http://www.newsdire.com/lifeandstyle/2684-saudi-seeks-45000-new-ethiopian-maids-per-month.html

[xiii] http://www.ophi.org.uk/wp-content/uploads/Ethiopia.pdf; 2010 Oxford Poverty and Human Development Initiative (OPHI).

[xiv] http://www.genocidewatch.org/alerts/countriesatrisk2011.html Current Countries at Risk of Genocide

[xv] http://www.terrorismwatch.org/2011/09/wikileaks-ethiopia-bombs-itself-blames.html

[xvi] xviii http://www.civicus.org/csw_files/CIVICUSAnalysisEthiopiaCharitiesProc160908.pdf

[xvii] *http://www.law.northwestern.edu/humanrights/documents/EthiopiaCSOPaper-Nov2009.pdf*